የዩናይትድ ስቴትስ የሰብአዊ መብቶችና ዴሞክራሲ ስትራቴጂ
ሰብአዊ መብቶችንና ዴሞክራሲን ማገዝ፣ የ1996/1997ቱ የዩናይትድ ስቴትስ ሬኮርድ
በዴሞክራሲ፣ በሰብአዊ መብቶችና በሠራተኛ ጽ/ቤት ይፋ ተደረገ

ዩናይትድ ስቴትስ በፕሬዚዳንት ቡሽ እና በኮንግሬስ አመራር ስር፣ ነፃነትን ማራመድ የውጭ ፖሊሲዋ ጠንካራ መሰረት አድርገዋለች፡፡ የፕሬዚዳንቱ ርእይ የሆነችው ነፃነት የነገሠባት ዓለም ባሳለፏቸው የሥልጣን ዓመታት የተገለፀ ቢሆንም፣ በቅርቡ ለሁለተኛው የአገልግሎት ዘመን መጀመሪያ እና ለስቴት ኦቭ ዚ ዩኒየን ባደረጓቸው ንግግሮች ላይ እንደገለፁት፣ በሚገባ ተገልጾ አያውቅም፡፡ ይኸው ርእይ ተግባራዊ በሚሆንባቸው መሣሪያዎቻችን በውጭ ጉዳይ ሕጎቻችን ርእዩ በግልፅ ይንፀባረቃል፡፡ ነፃነትና የሰው ልጅ ክብር የማይነጣጠሉ ናቸው፡፡ ፖሊሲዎቻችን ነፃነቶችን በማስፋት ያተኮሩበትም ከዚህ በመነሳት ነው፡፡ ዴሞክራሲንና ሰብአዊ መብቶችን የማጠናከር ፖሊሲያችን የሚመነጨውም ከአሜሪካዊ ሕልማችንና ከብሔራዊ ጥቅማችን ነው፡፡ ይህን ፖሊሲ የምንከተለው ትክክለኛ ስለሆነና ለኢፍትሃዊነት፣ ለሽብርተኝነት፣ ለኃይል አመጽና አለመረጋጋት አስተዋጽኦ የሚያደርጉትን ፍርሃትን፣ ጥላቻንና መበላለጥን ስለሚያስቀር ነው፡፡

በዓለም ሁሉ ዴሞክራሲን ለማስፋፋት ዩናይትድ ስቴትስ አያሌ ሀብትና ጉልበት ታፈስሳለች፡፡ በውጭ ፖሊሲያችን የተለያዩ ዘርፎች እነዚህ ዴሞክራሲን ወደፊት የማራመድ ተግባሮቻችን ይዋህዱ ዘንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መሪ ድርሻ አለው፡፡

ዩናይትድ ስቴትስ የውጭ ፖሊሲ ዓላማዋን ለመተግበር አያሌ ዲፕሎማሲያዊ፣ መረጃዊና ኢኮኖሚያዊ ዘዴዎችን ትጠቀማለች፤ በዚህም የሰብአዊ መብቶችንና የዴሞክራሲ ስልቷን ትተገብራለች፡፡ የአሜሪካ ባለሥልጣናት በመላው ዓለም ከመንግሥታት፣ ከብዙሀ ድርጅቶች፣ ከዓለማቀፍ ድርጅቶች፣ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ከግለሰቦች ጋር በመገናኘት የሰብአዊ መብቶች አያያዝ እንዲሻሻልና ወደ ዴሞክራሲ የሚደረገውን ሽግግር ያበረታታሉ፡፡

ዓመታዊው ሀገራዊ የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ዘገባ፣ ዓለማቀፉ የሃይማኖት ነፃነት ዘገባ እና ይህ ዘገባ፣ የመረጃዊ ዘዴዎች ምሣሌዎች ናቸው፡፡ ዩናይትድ ስቴትስ፣ የሰብአዊ መብቶችንና ዴሞክራሲን ለማስፋፋት ለሚታገሉ አገሮችና ድርጅቶች፣ በሁለትዮሽና በባለብዙ ዘርፍ መርሃ ግብሮች ጨምሮ በዓለም ባንክና በዓለማቀፍ ገንዘብ ድርጅት በመሳሰሉ ተቋማት በኩል፣ የኢኮኖሚ፣ የፋይናንስና የቴክኒክ እርዳታ ትሰጣለች፡፡

የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር መርሃ ግብሮች፣ ለዜጐች ተጠያቂ የሆኑና የዜጎች ችግር ተሰምቷቸው ምላሽ የሚሰጡ ዴሞክራሲያዊ መንግሥታትና ተቋማት እንዲያድጉና አቅማቸው እንዲበረታ ቴክኒካዊ ድጋፍንና ሌሎች እርዳታዎችን ይለግሳሉ፡፡ እነዚህ ፕሮግራሞች የዴሞክራሲ ግንባታ ጡቦች ሆነው በሚቆጠሩ ዋና ፅንሰ ሃሣቦች ዙሪያ ይሰናዳሉ፡፡ የዴሞክራሲ መርሃ ግብሮች የሕግ ልእልናን፣ ሰብአዊ መብቶችን፣ ውድድር የሚታይበት የፖለቲካ ሂደትን ከግልጽና ፍትሃዊ ምርጫ ጋር ያጣመረ ስርዓትን፣ ግልፅና ነፃ መገናኛ ብዙኃን ያለበት ሁኔታን፣ ጠንካራ የሕዝብ ማህበራትን፣ በመስተዳድራዊ ሥራ ሰፊ የዜጐች ተሳትፎን፣ ቀልጣፋ መስተዳድራዊ መዋቅሮችን፣ ተጠያቂነትንና በጎ ምላሽን ያስፋፋሉ፡፡

ዩናይትድ ስቴትስ ለለውጥ በጎ ፈቃድ ለሚያሳዩ መስተዳድሮች ለጥረቶቻቸው ቴክኒካዊና ፖለቲካዊ ድጋፍ ትሰጣለች፡፡ የዩናይትድ ስቴትስ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ የኖረ መመሪዋ እንደመሆኑ መጠን ይህን በጎ ፈቃድ ለማያሳዩ መስተዳድሮች የምትሰጠውን ድጋፍ ለማቋረጥ፣ ወይም አንድ ሀገር በሰብአዊ መብቶች አያያዙ ረገድ ያሉትን ድክመቶች ለማረምና ወደፊት ለማራመድ በጎ ፈቃድ ሲጎድለው፣ ዩናይትድ ስቴትስ እንዲህ ያሉ ድጋፎች ከመስጠት ልትቆጠብ ትችላለች፡፡ በሁለቱም ሁኔታዎች በሕብረተሰቡ ውስጥ ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለዴሞክራሲው ሂደት አዎንታዊ ጥረት ከሚያደርጉ ጋር ዩናይትድ ስቴትስ አብራ ትሠራለች፣ ድጋፏንም ትሰጣለች፡፡ የጊዜውና የዘዴዎች አመራረጥ ለየሁኔታው እንዲስማማ ተደርጐ ነው፡፡ የፕሬዚዳንቱን የውጭ ፖሊሲ ግቦችን በበለጠና በተሻለ መንገድ ተግባራዊ ሊያደርግ ይችላል የተባለውን ዘዴ ወይም የዘዴዎችን ቅንብር በተግባር እናውላለን፡፡ በጉዳዩ ላይ የወጡትን ድንጋጌዎች http://www.state.gov/g/drl res/42314.htm. በተባለው ድረ ገጽ ማግኘት ይቻላል፡፡

መንግሥታት የዜጎቻቸውን ነፃነት መግፈፍ እስኪያቆሙና ዜጎችም በራሳቸው መንገድና ነፃ ፈቃድ እነዚህን ነፃነቶቻቸውን እንዳይገፈፉ የሚያስችሉ ጠንካራ ተቋማትን እስኪመሰርቱ ድረስ፣ ለሰብአዊ መብቶች መጠበቅ የምናደርገው ትግል ይቀጥላል፡፡ ይህ ትግል እጅግ ከባድ ቢሆንም የዴሞክራሲን መርህና ተግባር ከፍ አድርገን ለመራመድ ቁርጠኝነታችን አይለወጥም፡፡ እንደአማሪካዊያን በአንድነት በመስራትና ከዴሞክራሲ ማህበረሰቦች ጋር በመተባበር በዓለም ላይ ሁሉ ለሚገኙ ሰዎች የሚሆን የነፃነት መንገድ እንቀድዳለን፡፡

መጋቢት 19/1997 ዓ.ም ይፋ ሆነ

አፍሪካ

ሰብአዊ መብቶችንና ዴሞክራሲን ማገዝ፣ የ1996/97ቱ የዩናይትድ ስቴትስ ሬከርድ በዲሞክራሲ፣ በሰብአዊ መብቶችና በሠራተኛ ጽ/ቤት ይፋ ተደረገ

«አፍሪካ፣ 1997/98 ዓ.ም ለአህጉሪቱ ለራሷ፣ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና ለዓለም ሁሉ አዲስ ምዕራፍ የሚከፈትበት ዓመት እንደሚሆን ለማረጋገጥ የማይተካ ድርሻ አላት፡፡»

ይህን ያሉት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ኮፊ አናን የሺህኛው ዓመት የልማት ግቦችን አስመልክተው በናይጄሪያ - አቡጃ ባደረጉት ንግግር ነው፡፡

ዩናይትድ ስቴትስ፣ ከሳህራ በታች ባሉ ሀገሮች ሁሉ ነፃ ፕሬስን የመሳሰሉ ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን የሚያበረታቱ፣ በዴሞክራሲያዊው ሂደት ውስጥ ተሳትፎው እንዲስፋፋ የሚያግዙ ተነሳሽነቶችን ትደግፋለች፡፡ መርሆችን ማራመድ በተመለከተ፣ ዩናይትድ ስቴትስ ከአፍሪካ መንግሥታት ጋር በምታደርገው ግንኙነት ሁሉ ቀዳሚ ስፍራ የሚይዙት ዴሞክራሲና ሰብአዊ መብቶች ናቸው፡፡ ዩናይትድ ስቴትስ በዴሞክራሲና በሰብአዊ መብቶች አያያዝ መልካም ስም ያላቸው አገሮች በአካባቢዋ እንዲሁም በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤና ጂኒቫ በሚገኘው የመንግሥታቱ ድርጅት የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽንን በመሰሉ አካላት ውስጥ አርአያነታቸው ጉልህ ሆኖ እንዲታይ ታበረታታለች፡፡

አፍሪካ ግሮውዝ ኤንድ ኦፖርቺኒቲ አክት (አጐዋ)፤ ዩናይትድ ስቴትስ በአፍሪካ ለምትከተለው ፖሊሲ እምብርት ነው፡፡ ድንጋጌው ለዴሞክራሲና ለሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል፡፡ አጎዋ የዴሞክራሲ ጥያቄዎችን ለመመለስ፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን፣ ሰብአዊ መብቶችንና የሠራተኛ መብቶችን ለመጠበቅ ያልተቋረጠ ጥረት ለሚያደርጉ አገሮች፤ ለንግድ ልውውጥ ጥቅሞች ዋስትና በመስጠት ዴሞክራሲያዊ አስተዳደርን ያበረታታል፡፡

የውጭ እርዳታ አሰጣጥን ቅደም ተከተል ለመወሰን በፕሬዚዳንት ቡሽ ተነሳሽነት የተነደፈው የሺህኛው አመት ተግባራት የውጤት መመዘኛ (ዘ ሚሊኒዬም ቻሌንጅ አካውንት) ዘዴ፣ ከዚህ ቀደም ታይተው በማያውቁ የእርዳታ መርሃ ግብሮች አፍሪካን ተጠቃሚ ያደርጋታል፡፡ በዚህ ሁሉ አቀፍ በሆነ አሠራር አማካይነት የሰብአዊ መብቶችን በሚያከብሩ መስተዳድሮች የሚገዙ አገሮች በዓለም ሁሉ እየተስፋፋ የሚገኘው የነፃነት ማእበል እንደሚሰማቸው ዩናይትድ ስቴትስ እርግጠኛ ናት፡፡

በጋና፣ በቦትስዋና፣ በሞዛምቢክ፣ በናሚቢያ እና በማሊ የተካሄዱት ተከታታይ ምርጫዎች፣ የአፍሪካ ሕዝቦች የሰብአዊ መብቶችን የሚያከብሩና ለመረጣቸው ሕዝብ ተጠያቂነት ያላቸው መስተዳድሮችን ለመምረጥ እንደተዘጋጁ ጠንካራ መልእክት አስተላልፈዋል፡፡

በ1997 ታህሣሥ ወር ላይ፣ የሱዳን መስተዳድርና የሱዳን ሕዝብ የነፃነት ንቅናቄ/ሠራዊት በመደራደርና በመጨረሻም ስምምነት በመፈራረም ለሁለት አሠርት የዘለቀውን የእርስ በርስ ጦርነት አቁመው ወደ ሰላም ደርሰዋል፡፡ ይሁንና በ1996 በሐምሌና በነሐሴ ወራት ውስጥ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በዳርፉር የተቀሰቀሰውን ጦርነት በመሸሽ፣ በቻድና በሱዳን ድንበር መካከል ባሉት የመጠለያ ካምፖች ከሰፈሩት ስደተኞች መረጃ የሚያሰባስብ ቡድን ወደ ዳርፉር

ልኳል፡፡ በከፊል ይህ ቡድን ያሰባሰበውን መረጃ መሠረት በማድረግ፣ ባለፈው መስከረም ወር 1997 የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኮሊን ፖዌል በዳርፉር የሚፈፀመውን አመፅ (የኃይል እርምጃ) «የዘር ማጥፋት» ድርጊት እንደሆነ ሲበይኑ «የሱዳን መስተዳድርና ጃንጃዊዶች ለዚህ ተጠያቂ ናቸው» ሲሉ ገልፀዋል፡፡ በዳርፉር የሚገኘውን የደህንነትና የሰብአዊ መብቶች ሁኔታን ለማሻሻል ዩናይትድ ስቴትስ አያሌ ሀብት አፍስሳለች፡፡

በዚምባቡዌ ሕዝባዊ ማህበራት፣ መገናኛ ብዙኃንና የፖለቲካ ተቃዋሚ ቡድኖች፣ ለዴሞክራሲያዊ ለውጦችና ለመሠረታዊ ሰብአዊ መብቶች መከበር የሚያደርጉትን ትግል ቀጥለውበታል፡፡ በኮትዲቯር መንግሥት ቀደም ሲል በራሱና በተቃዋሚዎች መካከል የተፈረመውን የሠላም ማእቀፍ ስምምነት እንዲያከብር፣ የአፍሪካ ሕብረትና ዓለማቀፉ ሕብረተሰብ በመንግሥት ላይ የሚያሳድሩትን ተጽእኖ እንደቀጠሉበት ናቸው፡፡

እነዚህን አስቸጋሪ ሁኔታዎች ለመፍታት ዩናይትድ ስቴትስ ከሰሃራ በታች ካሉ ሀገሮች ጋር በመተባበር የምትሠራውን ሥራ ትገፋበታለች፡፡ ቀደም ሲል ከተከናወኑት ተቋማዊ ለውጦችና ተከታታይ የልማት ተግባራት የአፍሪካ ሕዝቦች ተጠቅመዋል፡፡ የአፍሪካዊያን የማያወላውል ቁርጠኝነትና የዩናይትድ ስቴትስ እርዳታ ዴሞክራሲንና የሰብአዊ መብቶችን መሠረት ያጠናክራል፡፡

<u>ኢትዮጵያ</u>

የኢትዮጵያ መስተዳድር (መንግሥት) ሲከተል የቆየውን የዘውጌ (የጎሣ) ፌዴራሊዝም መሠረት በማድረግ በ1996ም ሥልጣንን ከማእከል ወደ ክልልና ወረዳ ደረጃ ማውረዱን ቀጥሎበታል፡፡ የጎሳ ግጭቶች፣ የሰለጠነ የሰው ኃይል ችግር እና ለዲሞክራሲ ፅንሰ ሃሣቦች እንግዳ መሆን፣ ሂደቱን ውስብስብ አድርጐታል፡፡ የሰብአዊ መብቶች አያያዝ በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቂት መሻሻል ቢታይም አሁንም ብርቱ ችግሮች አሉ፡፡ የፌዴራልና የአካባቢ ፖሊስ ኃይሎች ተገቢ ሥልጠና የላቸውም፤ ስለሆነም ያልተመጣጠነ ኃይል በመጠቀማቸው አያሌ ግድያዎችን በተለያየ ጊዜ ፈጽመዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ የዘፈቀደ እስርና ይዞ ማቆየት ይፈፀማል፡፡ የሕግ ተርጓሚው አካል በተደራረቡ ጉዳዮች በመጫኑና ብቃትም ስለሚጎድለው ሳይፈርድባቸው በእስር የሚንገላቱትን ዜጎች ቁጥር ከፍ አድርጎታል፡፡ መስተዳድሩ የመሰብሰብንና የፕሬስን ነፃነት መገደቡን ቀጥሎበታል፡፡ መንግሥት፣ በሰው ልጅ የሚፈፀምን ንግድ ለማስቆም አንድ ኃይለ-ግብር ቢያቋቁምም፤ በሰው ልጅ የሚከናወን ንግድ፣ በሴቶች ላይ የሚፈፀመው የኃይል ጥቃትና መድልዎ ዛሬም ብርቱ ችግሮች ናቸው፡፡ የዩናይትድ ስቴትስ ኤምባሲ ባለሥልጣናት፣ ገንቢ የሆኑ የመፍትሔ መፈለጊያ ዘዴዎችን ለማግኘት ይረዳቸው ዘንድ፣ ከመንግሥት ባለሥልጣናት፣ ካገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መሪዎች፣ ከተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችና ከሌሎች ኤምባሲዎች ጋር ተመካክረዋል፡፡ ዴሞክራሲንና ሰብአዊ መብቶችን ለማራመድ፣ ዩናይትድ ስቴትስ ከምትጠቀምበት አንዱ የስትራቴጂ አላባ፣ የመንግሥታትን እና የማህበረሰብ መሪዎችን አቅም መገንባት ነው፡፡ አውደ ጥናቶች፣ ሴሚናሮችና ሥልጠናዎች የዚህ አላባ ሆሄያት ናቸው፡፡

ዴሞክራሲንና የፖለቲካ ነፃነቶችን ለማስፋት በሚደረገው ጥረት ኤምባሲው ከሌሎች አገሮች ኤምባሲዎች ጋር በመሆን፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የገዥው ፓርቲ አባላት በአባሎቻቸው

ላይ ያደርሳሉ ያሉት የማዋከብ ተግባርን በተመለከተ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድንና የአካባቢ ባለሥልጣናትን አነጋግረዋል፡፡ ዩናይትድ ስቴትስ በመጪው ግንቦት 1997 ለሚደረገው ሀገር አቀፍ ምርጫ የሚካሄደው ዝግጅት ያሳደረባትን ፍላጐት ግልፅ ለማድረግ አምባሳደሯ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ጋር ተነጋግረዋል፡፡ በምሥራቅ ኢትዮጵያ የአንዳንድ ወረዳዎችን ክልላዊ ይዞታ ለመወሰን በወረዳዎቹ ውስጥ ተካሂዶ የነበረውን ውሳኔ ሕዝብ ለመታዘብ የኤምባሲው ተወካዮች ወደዚያው ተጉዘው ነበር፡፡ የገዥው ፓርቲ ካድሬዎች፣ ከዚያም በኋላ የፖሊስ ኃይሎችና ሌሎች፣ በተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ላይ ይፈፅማሉ የሚባሉትን ሕገወጥ እስራቶች፣ የማዋከብና የማሰቃየት ክሶች በተመለከተ የተቃዋሚ ፓርቲዎች መሪዎችና የኤምባሲው ባለሥልጣናት ተገናኝተው ተነጋግረዋል፡፡

የ1996ቱ የዩናይትድ ስቴትስ ምርጫ ዴሞክራሲን በተመለከተ እጅግ በጣም ጥሩ የትምህርት መድረክ ከፍቷል፤ ትምህርታዊ መድረኩ ያገለገለው በዋና ከተማዋ ለሚገኙ ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ጨምሮ ለሀገሪቱ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ልሂቃን ነበር፡፡ ለጋዜጠኞች ሥልጠና በመስጠትና አዲሱን የፕሬስ ሕግ ረቂቅ በተመለከተ በተሰጠው ምላሽ ከአለማቀፍ ማህበረሰቡ ጋር በመተባበር ያደረገው አስተዋጽኦ፣ ኤምባሲው ለሀገሪቱ የፕሬስ ነፃነት ጠንካራ ድምፅ ሆኗል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሀገሪቱን የዳኝነት ሥርዓት አቅም ለመገንባት የነደፈውን መርሃ ግብር፣ ዩናይትድ ስቴትስ በገንዘብ እየረዳች ትገኛለች፡፡ በ1996 ዓ.ም የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የኢትዮጵያን ፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ በተመለከተ፣ ለ1,157 የጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኞች፣ እንዲሁም ለ15 የአዲስ አበባ መዘጋጃ ቤት ዳኞች ሥልጠና ሰጥቷል፡፡ መርሃ ግብሩ ከተጀመረ ወዲህ 226 ሴት ዳኞችን ጨምሮ በመላ ሀገሪቱ ከ3000 ዳኞች በላይ በመርሃ ግብሩ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

በ1996 ዓ.ም በአጠቃላይ 13 የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብቶች ፕሮጀክቶችን ኤምባሲው በገንዘብ ረድቷል፡፡ ለምሳሌ ያህል፤ በአንዱ ፕሮጀክት አማካይነት፣ የአዲስ አበባው የሙስሊም ሴቶች ማህበር፣ በምሥራቅ ኢትዮጵያ ለሚኖሩ የአፋር ሴቶች፣ ከኢትዮጵያ ሕገ መንግሥትና ከሼሪአ ሕግ አኳያ ሴቶች ያላቸውን መብት በተመለከተ ግንዛቤ ለማስጨበጫ የሚረዱ ተከታታይ አውደ ጥናቶችና ውይይቶችን እንዲያካሂድ አስችሎታል፡፡

አምባሳደሯና ሌሎች የኤምባሲው ባለሥልጣናት፣ በተለያዩ ንግግሮችና ሕዝባዊ መድረኮች በሚሰጧቸው አስተያየቶች ለሰብአዊ መብቶች ጥብቅ ተሟጋቾች ነበሩ፡፡ አምባሳደሯ፣ ሰብአዊ መብቶችን የሚጥሱ መንግሥታዊ እርምጃዎችን በተመለከተ ማብራሪያዎች እንዲሰጧቸው ባለሥልጣናቱን (አንዳንድ ጊዜ በግል) ጠይቀዋል፡፡

በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአፍሪካ ጉዳዮች ጽ/ቤት ረዳት ሚኒስትር ኮንስታንስ ኒው ማንንና የዩናይትድ ስቴትስ ዓለማቀፍ የልማት ባለሥልጣን አስተዳዳሪ አንድሪው ናትሲዮስን ጨምሮ ኢትዮጵያን የጎበኙ የዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት ባለሥልጣናት የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትርንና ውጭ ጉዳይ ሚኒስትርን ጨምሮ ከአገሪቱ ባለሥልጣናት ጋር ባደረጓቸው ውይይቶች የሰብአዊ መብቶችን አያያዝ ጉዳይ አንስተዋል፡፡

የጎሳ ግጭቶችን አስመልክቶ ኤምባሲው በተለያዩ ደረጃዎች የኢትዮጵያን መንግሥት ባለስልጣናት አነጋግሯል፤ በታህሳስ ወር 1996 በጋምቤላ ተከስቶ የነበረውን ግጭት ተከትሎ ጉዳዩ በጥንቃቄ እንዲመረመር ከፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር ጋር ውይይት ተደርጓል፡፡ በዚሁ ዓመት የምርመራውን አካሄድ በቅርብ ከመከታተል ጎን ለጎን፣ ኤምባሲው ከፌዴራል እና ከአካባቢው መስተዳድር ጋር በመሆንና የአካባቢውንና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን አቅም በመገንባት፣ ግጭቶች እንዳይነሱ ለመከላከልና ከተነሱም ጉዳታቸው የሚቀንስባቸውን ብልኃቶች ለማሳደግ የሚያስችሉ መርሃ ግብሮችን ጀምሯል፡፡ የኢትዮጵያን ፌዴራል ፖሊስ ለማሰልጠንና ቴክኒካዊ እገዛ ለመስጠት፣ ኤምባሲው የገንዘብ እርዳታ አድርጓል፡፡ የገንዘብ እርዳታው፣ የፌዴራል ፖሊስ ምልምሎቹን መሠረታዊ የፖሊስ ክሂል የሚያስጨብጥባቸውን ፕሮጀክቶች በመንደፍና በማቋቋም አቅሙን ለመገንባት ይውላል፡፡ ክሂልን መሠረት ያደረገው የምልምል ፖሊስ ስልጠና ፕሮጀክት፣ የፖሊስ ሥነ ምግባርንና የሰብአዊ መብቶች አያያዝ መመዘኛዎችን ያጠቃልላል፡፡ የዩናይትድ ስቴትስ የገንዘብ እርዳታ፣ ዜጎችንና ፖሊስን ወደ ሚያቀራርበው ወደ ማህበራዊ ፖሊስ አደረጃጀት ያዘነበለ እንዲኖረው የሚደረገውን ጥረት ያግዛል፡፡ የኢትዮጵያ ሕግ አስፈጻሚ ባለሥልጣናት በዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት በሚደገፈውና የገንዘብ እርዳታ በሚደረግለት ጋቦሮኔ በሚገኘው ዓለማቀፍ ሕግ የማስፈፀም አካዳሚ የሰብአዊ መብቶች ሥልጠናን እንደ ጥናታቸው አንድ ክፍል ሆኖ ይሰጣቸዋል፡፡

በዩናይትድ ስቴትስና በኢትዮጵያ መካከል ካለው ወታደራዊ ትብብር አንድ ክፍል ሆኖ፤ የዩናይትድ ስቴትስ የሥልጠና መርሃ ግብር፣ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ መከላከያ ኃይል የጦርነት ሕግና የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ስልጠና በሰላም ማስከበር ስልጠና ውስጥ ይሰጣል፡፡ በዩናይትድ ስቴትስና በአፍሪካ የመጠባበቂያ ተግባራት ሥልጠናና ትብብር መርሃ ግብር ሥር፣ የዩናይትድ ስቴትስ ኮንትራክተሮችና ወታደሮች፣ በአሁኑ ጊዜ በላይቤሪያና በቡሩንዲ የሚገኙትን የኢትዮጵያ የመላከያ ሠራዊት አባላትን ጨምሮ አራት የብሔራዊ መከላከያ ኃይል ባታሊዮኖችን አሰልጥነዋል፡፡ በኤች አይ ቪ/ኤድስ ላይ ያለውን ግንዛቤ ከፍ ለማድረግ የሚካሄደውን ጥረት ለማገዝ የዩናይትድ ስቴትስ አምባሳደር ከሃይማኖት መሪዎች ጋር መደበኛ በሆነ መልኩ በተደጋጋሚ ተገናኝተዋል፡፡ ኤምባሲው በዚህ ረገድ፣ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን፣ ከመካነ ኢየሱስ ቤተክርስትያን፣ ከኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተክርስትያንና ሚኒስትሪ ኦቭ ቻሪቲ ሲስተርዝ ጋር በመተባበር የኤች አይ ቪ/ኤድስ መርሃ ግብሮችን ለማገዝ ሠርቷል፡፡

ከኢትዮጵያ ወደመካከለኛው ምስራቅ በሴቶችና በሕፃናት ላይ የሚካሄደውን ንግድ ለመዋጋት የዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት ተጨባጭ እርዳታ እያደረገ ይገኛል፡፡ ከዚህም አንዱ በዓለማቀፍ የማይግሬሽን ድርጅት በኩል የሚሰጠው የገንዘብ እርዳታ በአዲስ አበባና ለሌሎች አካባቢዎች የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በሰው ላይ የሚደረገው ንግድ ምን ያህል አደገኛ እንደሆነ የሚሰጠውን ትምህርት በቅርብ መከታተል ነው፡፡ ይህን ፕሮጀክት ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ዓለማቀፉ ድርጅት ዳተኝነትን ተመልክቷል፡፡ ባለፈው ዓመት ከታዩት ውጤታማ ክንውኖች መካከል፣ ሕገወጥ ሥራ አፈላላጊዎችን በተመለከተ ሕዝቡ ትምህርት የሚያገኝበት የሬዲዮ ፕሮግራም መጀመሩ፣ ከውጭ ለተመለሱ ጉዳተኞች እርዳታ መለገስና በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር አማካይነት በውጭ አገር ተቀጥረው ለመሥራት ለሚፈልጉ

የምክር አገልግሎት መስጠት ይገኙበታል፡፡ 24 ሰዓት ሙሉ ክፍት በሆነ የስልክ መስመር ምስጢራዊ የምክር አገልግሎት እና መረጃ የመሰጫ ስርአትም ተዘርግቷል፡፡

መንግሥት በማደጎ ድርጅቶች ላይ ጥሎ የቆየውን እገዳ እንዲያነሳ ኤምባሲው ተጽእኖ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ይኸው ጥረት ፍሬ አፍርቶ መንግሥት ለሁለት የማደጎ ድርጅቶች ፈቃድ በመስጠት ለሕገወጥ የማደጎ ደላሎች ትልቅ እንቅፋት ፈጥሯል፡፡ ኤምባሲውና መንግሥት ሕገወጥ የማደጎ አሠራርን በመከላከል ረገድ በጣም ጥሩ የሥራ ግንኙነት አላቸው፡፡ ኤምባሲው አንድ ተጠርጣሪ ሕገወጥ የማደጎ ደላላ ሲያገኝ፣ መንግሥት አቅሙ ውሱን ይሁን እንጂ፣ ምርመራ አካሂዶ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የደላላውን ሥራ እንዲቆም ያደርጋል፡፡

የዩናይትድ ስቴትስ መንግሥትና በየአገሮቹ የሚገኙ የበሽታ መቆጣጠሪያ ማእከሎች ከአስተናጋጅ መንግሥታት ባለሥልጣናት ጋር በመሆን ከኤች አይ ቪ /ኤድስ ጋር በሚኖሩ ሰዎች ላይ የሚደርሰውን መገለል ለማስቀረት በትብብር ሠርተዋል፡፡ የአለም የኤድስ ቀን በተከበረበት እለት፣ ችግሩን አጉልቶ ለሕዝቡ በማሳየትና ማግለል እንዲቀር ለማድረግ በአዲስ አበባ ለተከናወኑ አያሌ እንቅስቃሴዎች ኤምባሲው ድጋፍ ሰጥቷል፡፡